# ፍንትው ብሎ ታየ

እውነት ብትከሳም ፣ ብትመነምንም
እንደ ውሸት ገና ፣ ደንደሳም ባትሆንም
ጊዜዋን ጠብቃ ፣ የማታ የማታ
አልተሸነፈችም ፣ በውሸት ተረትታ
ሃሰት ተዘረረች ፣ በእውነት ተገፍታ ።

ጠልፋ ስትጥለው ፣ በገዛ ምላሱ
ድንጋይ መፈንቀሉን ፣ መሮጥ መልከስከሱ
መድሃኒት ፍለጋ ፣ ቅጠል መበጠሱ
እውነትን ለመቅበር ፣ አይቀር ትርምሱ
ቀን እንደጨለመ ፣ ባያውቀውም እሱ ።

በነጋ በጠባ ፣ አስር በመለቅለቅ
ምሁር ነኝ እያሉ ፣ ትግል ማጨማለቅ
የህዝብ ወገን መስሎ ፣ ሁሉን ማንቦጫረቅ
ዘር ብሎ ከጀርባ ፣ በስለት መሰቅሰቅ
የሚቻል አልሆነም ፣ እራስን መደበቅ
በሃሰት ዲሪቶ ፣ መታጀል ለማይሞቅ
የሚበጀው ይልቅ ፣ ከራስ ጋር መታረቅ ።

እዚያው ወያኔ ስር ፣ ሆነው ከብብቱ
በይስሙላ ብቻ ፣ ሞቱን ሲያሟረቱ
እውነተኛን ታጋይ ፣ በሾኬ እየመቱ
በዲሞክራሲ ስም ፣ ምለው ሲገዘቱ
ቀስ በቀስ ታወቀ ፣ ሁሉም ማንነቱ
አደባባይ ወጡ ፣ ሲመጣ መንግሥቱ ።

መሰረቱ ታየ ፣ የቆመበት ግንዱ
የደርግ እንግዴ ልጅ ፣ እንደሆን ትውልዱ
በህዝብ እየማሉ ፣ በህዝብ የነገዱ
ከላይ ታች እያሉ ፣ ኖረው ሲሸውዱ
ፍንትው ብሎ ታየ ፣ የሸሸጉት ጉዱ
ምርቱ ተንጠርጥሮ ፣ ተለየ ከግርዱ ።

ታዛቢው . . . February 14, 2012